ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ | ሰፈር 26/1440 ሂ.
አውቃፍ ሚኒስትር | ኦገስት25/2019 ግ.

## ይህ ነው እስልምና ማለት

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَاتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَاتَّخَذَ اللَّهُ إِبْرَاهِيمَ خَلِيلًا }

ለአለው ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እርሱ መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲኾን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን ነው አላህም ኢብራሂምን ፍጹም ወዳጅ አድርጎ ያዘው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

### ከዚህም በመቀጠል፡

እውነተኛ እስልምና ማለት ለአላህ (ዐ.ወ.) ሙሉ በሙሉ እጅ መስጠት ለሱ መታዘዝና መገዛት ነው፡፡ እንድሁም እስልምና ማለት የአላህ መልክተኛ ሰይዲና ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) መውደድ፣ መከተልና እሳቸውንም አርአያ ማድረግ ነው፡፡ አሁንም እስልምና ማለት መልካም ምግባር፣ ለሱ መጋዛት፣ ለሱም ራስን ዝቅ ማድረግ፣ መንፈስ መልካም መሆን፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር የአለው እንቅስቃሴ ፈካ ባለ ፊት መሆን፣ እዝነትና ርህራሄ ማሳየት፣ አለመን መገንባትና ማነጽ፣ ስልጣኔና ልማትን ማስፋፋት ነው፡፡ እስልምና ተከታዮቹ በርጋታም ሆነ በእንቅስቃሴ እንድሁም በመላ ሥራዎቻቸው ጎልቶ የሚታይ የሕይወት ስርኣት ነው፡፡

የእስልምና እምነት ነገሮችን እንድናሻሻልና እንዲናድስ፣ ለዚህች ዓለምም ሆነ ለመጭው ዓለም የሚጠቅም ልማትን እንዲናከናውን የሚያዝ እንጂ በሃይማኖት ስም እንድናፈርስ የሚያዝ ሃማኖት አይደለም፡፡ እምነቱ ርህራሄ፣ ሰላምና ጸጥታ እንድሁም ሰላም በመላ የዓለማችን ክፍል እንዲሰፍን የሚሰብክ እምነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ} .

ትርጉሙም ((ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡)

ማለት ነው፡፡

በጅብሪል (ዐ.ሰ.) ሐዲስ የሰፈሩትን የእስልምና ማእዛናት የሚመራመር ሰው እነዚህ ማእዘናት ቅን የሆነን ሰው በመገንባት ታላቅ ሚና ያላቸው መሆኑን በትክክል ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ጅብሪል ከእለታት አንድ ቀን ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በመምጣት (ሙሐመድ ሆይ! እስኪ ስለእስልምና ንገረኛ በማለት ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (እስልምና ብሎ ማለት ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም እንድሁም ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው ብለህ መመስከርህ፣ ስግደትን ደንቡን ጠብቀህ ማድረስህ፣ ዘካን መስጠትህ፣ ረመዳንን የምትፆም መሆንህና ወደሱም ለመድረስ የምትችል ከሆነ የሐጅን ሥራ ማከናውነህ ነው) አሉ፡፡

አንድ ሰው አላህ አጋር የሌለው ብቸኛ ፈጣሪ መሆኑንና ሰይዲና ሙሐመድ የሱ ባሪያና መልክተኛ መሆናቸውን ሲገነዘብ ለአላህ በመታዘዝና እሱ መላ ተግባራቱን የሚቆጣጠር መሆኑን በእርግጠኝነት እምኖ ትእዛዙን ይፈጽማል፡፡ ከከለከለውም ነገር አጥብቆ ይርቃል ወሰን ከመተላለፍም ይታቀባል፡፡ የታዘዘውን ነገር ከመፈጸም አይቦዝንም፡፡ እንድሁም የሱ ያልሆነን ሙብት ለማግኘት አይሞክርም፡፡ ይህ ምእምን ነብያችንን (ሰ.ዐ.ወ.) መከተሉን ለማሳመር ይጣጣራል፡፡ እሳቸው ያደርጉ እንደነበረውም ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት በርህራሄ፣ በእዝነት፣ ራስን ዝቅ በማድረግና በለዘብተኝነት የታነጸ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡

ከእስልምና ማእዘናት ዋናው የሆነው ስግደት ከአጸያፊና ከተጠላ ነግር በመከላከልና በአላህ መንገድ ቀጥ ብሎ እንዲጸና በማድረግ ለአላህ ባሪያ ያለው ጥቅም እጅጉን ከፍተኛ ነው፡፡ ያን ጊዜም ማንኛውም ሙስሊም በራሱ መንፈስም ሆነ በማህበረሰቡ መካከል በሰላም ይኖራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{اتْلُ مَا أُوحِيَ إِلَيْكَ مِنَ الْكِتَابِ وَأَقِمِ الصَّلَاةَ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ} .

ትርጉሙም (ከመጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ፡፡ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡) ማለት ነው፡፡

ዘካንም መስጠት ከእምነትና ከሰብኣዊነት አንፃር ያለው ፋይዳ በጣሙን ከፍተኛ ነው፡ እሱ መንፍስን በቁሳቁስ ያለመጠን ከመተሳሰር ያድናል፡፡ በዚህም አንድ ሰው ገንዘብ ወደአንድ ነገር መድረሻ መሳሪያ እንጅ እሱ ራሱ መዳረሻ አለመሆኑን ይገነዘባል፡፡ ዘካን መስጠት ወደትብብር፣ መተዛዘንና የሌሎችን ስሜት ወደመገንዘብ የሚያደርስ በር ነው፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማህበረስብ ራሰወዳድነትም ሆነ አሉታዊነት የለበትም፡፡ ይህን ማለትም ሃይማኖታችን የስጦታ፣ የችሮታ፣ የመስዋእትነት፣ የመበዠት፣ ሰዎችን ከራስ የማስቀደም ሃማኖት ሲሆን ለኔ ብቻ ማለትን፣ ግበጋባነትንና ስስታምነትን አጥብቆ ይዋጋል፡፡ ምእምን ገራገር፣ ቸርና ለጋስ ሊሆን ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አንሷሮችን ሲያመስግናቸው እንድህ ብሏል፡

{وَالَّذِينَ تَبَوَّءُوا الدَّارَ وَالْإِيمَانَ مِنْ قَبْلِهِمْ يُحِبُّونَ مَنْ هَاجَرَ إِلَيْهِمْ وَلَا يَجِدُونَ فِي صُدُورِهِمْ حَاجَةً مِمَّا أُوتُوا وَيُؤْثِرُونَ عَلَى أَنْفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ وَمَنْ يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِ فَأُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ}.

ትርጉሙም (እነዚያም ከበፊታቸው አገሪቱን መኖሪያ ያደረጉት እምነትንም የለመዱት ወደእነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ፡፡ (ስደተኞቹ) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያገኙም፡፡ በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡ የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ እነሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ፆምም እንደዘለሁ የሙስሊምን መልካም ምግባር በማስተካከል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መልካም ምግባሩ ሲስተካከል አላህ (ዐ.ወ.) ዘውትር የሚሰራውን ሁሉለ የሚቆጣጠር መሆኑን ባለመዘንጋት መንፈሱን በትእግስተና መከራን በመቻል ይገራታል፡፡ አላህን ከሚያስቆጣ ነገርም ከፍ እንዲትል ያደርጋታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ፆም ጠባቂ ነው፡፡ አንዳችሁ ፆም በሚይዝበት ቀን ጽያፍ ቃል አይናገር ድምጹንም ከፍ አያድርግ አንድ ሰው ቢሳደበው ወይም ሊታገለው ቢመጣ

እኔ ፆም የያዝኩ ሰው ነኝ ይበል) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የሀሰት ቃልንና በሀሰት መሥራትን ያልተወ ሰው ለአላህ የሱ ምግብና መጠት መተው አያስፈልገውም፡፡)
ሐጅ ሥራውን ከማከናወኑ በፊት፣ በሚያከናውንበት ወቅትና ከፈጸመውም በኋላ የስነ ምግባርና የስርኣት ግዴታን መወጣት የሚጠይቅ ታላቅ ዒባዳ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ٱلحَجُّ أَشۡهُرٌ مَّعۡلُومَاتٌ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي الْحَجِّ وَمَا تَفْعَلُوا مِنْ خَيْرٍ يَعْلَمْهُ اللَّهُ وَتَزَوَّدُوا فَإِنَّ خَيْرَ الزَّادِ التَّقْوَىوَاتَّقُون يَا أُولِي الأَلْبَابِ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም፡፡ ከበጎም ሥራ የምትሠሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል፡፡ ተሰነቁም፤ ከስንቅም ሁሉ በላጬ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው፡፡ የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ፡፡) ማት ነው፡፡
(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ይላሉ፡ ‹እኔ የአላህ መልክተኛ እንድህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ (ሴትን ከመገናኘትና ከአመጽ ነፃ በሆነ መልኩ ሐጅን ያከናወነ ሰው እናቱ አንደወለደችበት ቀን (ንጹህ) ሆኖ ይመለሳል፡፡) በዚህ መልኩ ሁሉም የእስልምና ማእዘናት በማህበረሰቡ ደግን ነግር፣ ሰላምንና ደህንነትን በማስፈን ረገድ ስፊ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡
ቀጥተኛውን ሃይማኖታችንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የመልካም ምግባር ሃይማኖትና ተልእኮውም ይህን መልካም ምግባር የተሟላ ማድረግ መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (እኔኮ የተላኩት መልካም መግባርን የተሟላ ለማድረግ ነው፡፡) እውነት፣ ቃልን ማክበር፣ አመኔታ፣ መልካም ሥራ፣ ዝምድናን መቀጠል፣ ቸርነት፣ ለጋስነት፣ ሰውን መርዳት፣ አክብሮት፣ ሰብእነት፣ በሰዎች ላይ ተንኮል ከመፈጸም መታቀብ፣ እርዳታ የሚጠይቅን ሰው ማገዝ፣ ጭንቀትን ማቃለልና ለእንሰሳት ርህራሄ ማድረግ የሚሉት ተግባራት በሚፈጸሙበት ቦታ ትክክለኛው የእስልምና አላማ ተተግብሯል ማለት ይሆናል፡፡
የእስልምናን ስር መሰረት መገንዘብ፣ ገራገር የሆነውን የተልእኮውን ምስጢር ማወቅ አጅግ የላቁ የሆኑትን አላማዎቹንና ግቦቹን በጥልቅ መረዳት ይህንም ሁሉ ከዘመኑ አዳድስ ነገሮችና አስፈላጊነቱ ጋር አጣትሞ ገቢራዊ

ማድረግ የዘመኑን ተግዳሮቶች ለመቋቋም፣ የጸንፈኛ አሻባሪ ቡድኖችን ልጓም ለመግታት፣ አፈንጋጭ እሳቦቶችን እንዳይስፋፉ ለመከበብ፣ አንድሁም ደረቅ፣ ግትርና ዝግነት ከአለቸው አዙረቶች፣ ከተሳሳተ ግንዛቤና ከጠባብነት ለመውጣት፣ ከዚያም ሰፊ፣ ቀላል፣ በጣም በሳልና ንቃት ወዳለበት ዐለም ለመግባት፣ የህዝብና የሀገርን ጥቅም ለማስከበር፣ ሰላም፣ ደህንነትና ጸጥታን፣ መረጋጋትን ለማረጋገጥ፣ ለመላ የሰው ልጅ ደስታን እውን ለማደርግ ሰፊ ሚና ያለቸውን የላቁ የሰብኣዊ እሴቶችን ለማስፋፋት አመራጭ የሌለውና አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ማንኛውም ሙስሊም ሊያከናውነው የሚገባ ከሆነ ተቀዳሚ ግዴታና እጅጉን አስፈላጊ ከሆኑ ተግባራት ቅድሚያ የሚሰጠው ለሰዎች ሁሉ የእስልምና መልካም ገጽታዎችን አጉልቶ ማሳየት የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህውም የዓለም ህዝብ ሁሉ እስልምና የሰላም እምነትና ሰላም እንድሰፍን የሚገፋፋ ሃማኖት መሆኑን እንድገነዘብ ነው፡፡ ሰላም ከአላህ ባሕርይ አዘል ስሞች አንድኛው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ}

ትርጉሙም (እርሱ አላህ ነው፡፡ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ... ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና ሰላምታ ሰላም የሚል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንድህ ላል፡

{وَلَا تَقُولُوا لِمَنْ أَلْقَىٰ إِلَيْكُمُ السَّلَامَ لَسْتَ مُؤْمِنًا}

ትርጉሙም (ሰላምታንም ወደናንተ ላቀረበ ሰው የቅርቢቱን ሕይወት ጥቅም የምትፈልጉ ኾናችሁ ምእመን አይደለህም አትበሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ በጀነት የጀነት ሰዎች ሰላምታም ሰላም -የሚል- ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَالْمَلَائِكَةُ يَدْخُلُونَ عَلَيْهِم مِّن كُلِّ بَابٍ سَلَامٌ عَلَيْكُم بِمَا صَبَرْتُمْ فَنِعْمَ عُقْبَى الدَّارِ}

ትርጉሙም (መላእክትም በእነርሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ፡፡ ሰላም ለእናንተ ይኹን፡፡ (ይህ ምንዳ) በመታገሳችሁ ነው፡፡ የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር!» (ይሏቸዋል)፡፡ ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስግደት በኋላ በሚከተሉታ ቃላት አላህን ይጸልዩ ነበር፡

(اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلاَمُ ، وَمِنْكَ السَّلاَمُ ، تَبَارَكْتَ يا ذَا الْجَلاَلِ وَالإِكْرَامِ) .

ትርጉሙም( ጌታዬ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ ሰላምም ካንተ ነው፡፡ በረከትህ በዛ አንተ የሞገስና የማክበር ባለቤት የሆንህ ጌታ፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት የሰውን ልጅ ክብር ለማስጠበቅ ሃሜትን፣ አሉባልታን፣ መቅኘነትን፣ በቃልም ይሁን በተግባር ወይም ጣትን በመቀሰር ሰው ማንኳሰስን አጥብቆ ይጠላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَى أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَى أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ}**

ትርጉሙም (እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡
ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ወደወንድሙ በቁራጭ ብረት ያመለከተ ሰው ይህን ተግባሩን እስከሚያቆም ድረስ መላእክት ይረግሙታል፡፡ የናት ያባቱ ልጅ ወንድሙም እንኳን ቢሆን፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፊትን መምታትን እንድሁም በፊት ላይ ትኩሳት ማድረግን ከለክለዋል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ፊቱ ላይ የተተኮሰን እንሰሳ ባዩ ጊዜ (የተኮሰውን ሰው አላህ ከእዝነቱ ያርቀው አሉ፡፡)
ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) ስለአንድት ቀንን ጹዋሚና ሌሊትን ቋሚ ነገር ግን ጎረቤተቿን የምታሰከፋ ሴትዮ በተጤቁ ጊዜ የሰጡት መልስ ( እሷ በገሀነም ውስጥ ናት፡፡) የሚል ነበር፡፡ ነብያችን እንድህ ማለታቸው ተወርቷል፡ (በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ጎረቤቱን አያስከፋ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው እንግዳውን ያክብር፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር አለዚያም ዝም ይበል፡፡ )
ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትና በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰይዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ገራግሩ የእስልምና እምነት አስተምህሮ፣ መልካም ስነ መግባሮቹና የላቁ እሴቶቹ በባልደረቦቻቸው ልብ እንድሰርጹ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በመሆኑም በመጨረሻም አነዚህ አስተምህሮዎች ከሁሉም ሰው ጋር በአላቸው ግንኙነትም ሆነ በራሳቸው የእለት ከእለት ኑሮ ጎልቶ የሚታይ የሕይወት ስርኣታቸው ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጀዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብ ከሐበሻው ንጉስ ነጃሺ ፊት በቆሙ ጊዜ መጀመሪያ ለመግለጽና ለማብራራት የሞከሩት ከነዚህ እሴቶች ጥቂቶቹን ነበር፡፡ ሲያብራሩም እንድህ ብለዋል፡ ‹አንተ ንጉስ ሆይ! እኛ ታቦት የምንገዛ፣ በክት የምንበላ፣ ዝሙት የምንፈጽም፣ ዝምድንናን የምንቆርጥ፣ ጉርብትናን ፈጽሞ የማናከብርና ከኛ ጉልበተኛው ደካማውን የሚበላ የድንቁርና ሰዎች ነበርን፡፡

በዚህም ላይ እያለን ዘሩን፣ እውነተኛነቱን፣ ታማኝነቱን፣ ጥብቅነቱን የምናውቀውን ከኛ የሆነን መለክተኛ አላህ ወደኛ ላከ፡፡ አላህን በአንድ አምላክነቱ እንድንገዛው፣ ከሱም ሌላ ያለን እኛና አባቶቻችን እናመልከው የነበረውን ድንጋም ይሁን ጣኦት በኣድ አምላክን እርግፍ አድርገን እንድንተው ጥሪ አደረጉልን፡፡ በወሬያችን እውነተኞች፣ አደራ ጠባቂዎች፣ ዘምድን ቀጣዮች፣ መልካም ጎረቤቶች እንድንሆን፣ እርም ከሆኑ ነገሮችና ደመን ከማፍሰስ እንድንታቀብ አዘዙን፡፡ ጽያፍ እንዳንናገር፣ ሀሰት እንዳናወራ፣ የሙት ልጅ ገንዘብን ያላግባብ እንዳንበላና ንጹሃንን እንዳንዘልፍ ከለከለን፡፡ አንድ አላህን በሱ ማነንም ያለማጋራት እንድናመልክ፣ ስግደትን እንድናደርስ፣ ዘካንም እንድንሰጥ፣ ጾምንም እንድንጾም አዘዘን...›

እውነተኛ ሙስሊም አይዋሽም፣ አያታልም፣ አይከዳምም፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማለት ሰዎችን በምላሱም ሆነ በእጁ ተንኮል የማይጎዳ ሰው ነው፡፡ እውነተኛ ምእምን ማለተም ሰዎች በደማቸው፣ በክብራቸው፣ በገንዘባቸውና በሕይወታቸው እምነት የሚጥሉበት ሰው ነው፡፡ እውነተኛ ሙስሊም ማለት ከሱ ደግ ነገርና መልካም ሥራ እንጂ ወደሰዎች የማይደርስ በመሆኑ የእስልምና ሰነ ምግባር ገጽታ ጎልቶ የሚታይበት ሰው ነው፡፡

እውነተኛን ሙስሊም ግልጽ በሆነ ማብራሪያ ለማሳወቅ ብንፈልግ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰጡት ማብራሪያ የተሻለ መግለጫ አናገኝም፡፡ እሳቸው እንድህ ብለዋል፡ (ምእምን ማን እንደሆነ ልንገራችሁን? ምእምን ማለት ሰዎች በገንዘባቸውና በሕይዎታቸው እምነት የጣሉበት ሰው ነው፡፡ ሙስሊም ማለት ደግሞ ሰዎች ከእጁና ከምላሱ ተንኮል የዳኑ የሆነ ሰው ነው፡፡ ታጋይ ማለትም ለአላህ በመታዘዝ ቀጥ እንድትል ነፍሱን የታገለ ሰው ነው፡፡ ሀገሩን የተወ ስደተኛ ማለትም ኃጢአትንና ወንጀልን የተወ ሰው ነው፡፡)

የአስልምና ሃይማኖት ተልእኮ የሰብእነት፣ የጥበብ፣ የመቻቻል፣ የርህራሄ፣ የሰፊነትና የለዘብተኝነት ተልእኮ ነው፡፡ የሚበታትን ሳይሆን የሚያሰባስብ፣ የሚያለያይ ሳይሆን የሚዋህድ ተልእኮ ነው፡፡ እስልምና ማለት ሙሉበሙሉ ፍትህ፣ እዝነት፣ መቻቻል፣ ማግራትና ሰብእነት ማለት ነው፡፡ እነዚህን የላቁ የሆኑ አላማዎችን የሚያራምድ ሰው በእውነተኛ እስልምና መመሪያዎች እየተመራ ነው፡፡ ከነዚህ አላማዎች ጋር የሚፃረር ነገር የሚፈጽም ደግሞ ከትክክለኛዎቹ የእስልምና አላማዎችና ግቦች ጋር በሚጋጭ መመሪያ እየተመራ ነው፡፡

ጌታችን ሆይ! ለመልካም ጠባይ ምራን ወደመልካም ጠባይ የሚመራ አንተ እንጂ የለምና መጥፎ ጠባይንም ከኛ አርቅልን መጥፎ ጠባይንም የሚያርቅ ካንተሌላ የለምና፡፡ አንተ አዛኝና ርህሩህ ጌታ ሆይ! ሀገራችንና ህዝባችንን ጠብቅልን አሜን፡፡